በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# በፈጣኑ ዓለም ውስጥ የሚፈለግ ትዕግስት


መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**<u>E-mail:</u>** kesisolomon4@gmail.com


*<u>ቦታ፡-</u>* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**ጥር ፲፰ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.**

# በፈጣኑ ዓለም ውስጥ የሚፈለግ ትዕግስት

**ዓላማ**

- በምንኖርበት ፈጣን ዓለም ውስጥ ስለሚፈለገው ትዕግስትና በመታገስ ስለምናገኘው መንፈሳዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ መማር፡፡

**መግቢያ**

- የምንኖረው በፍጥነት በመጓዝ ላይ በሚገኝ ዓለም ውስጥ ነው፡፡
- በርካታ ሰዎች በፍጥነት ይወስናሉ ይናገራሉ ያሽከረክራሉ ያሰቡትንም በተቻለ ፍጥነት ለማሳካት ይሻሉ፡፡
- በዚህም ፍጥነት የተነሳ «ብንታገስ ከሌሎች ጋር የገጠመን ችግች ማስወገድ ከአደጋውም መትረፍ እንችል ነበር» በማለት የሚያለቅሱ በርካታዎች ናቸው፡፡
- የተሽከርካሪ አደጋ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ተከስቶ ውጤቱ የማያስደስትና ረጅም ጊዜም የሚቆይ ተጽኖ የሚያሳድር ነው፡፡
- በዚህ ዘመን የሚያስፈልገን ከመናገር ወይም ርምጃ ከመውሰድ በፊት ቆም ብሎ ማሰብ   በሌሎች ሳንናደድ ወይም ሁከት ሳንፈጥር በጽናት መታገስ አስፈላጊ ነው፡፡
- በፈጣኑ ዓለም ውስጥ በችኮላ ሳይሆን በትግስትና በጥበብ ሥራውን በመስራት እንድንመስለው የሚሻው እግዚአብሔር ነው፡፡

# በፈጣኑ ዓለም ውስጥ የሚፈለግ ትዕግስት

**እውነተኛ ታሪክ**

- አንድ ወጣት በአውቶብስ ቆሞ ይጓዝ ነበር፤ ያ ቀን ሙቀቱ ከፍተኛ የነበረበት እና አውቶቡስ ጢም ብሎ የሞላበት ቀን ነበር፡
- ይህ ወጣት በጉዞ ላይ ሳሉ አንድ ጥንካሬ ያለው ነገር ጎኑን ደጋግሞ ሲወጋው ተሰማው፡፡
- ሆን ብሎ የተደረገበት ስለመሰለው እጅግ ተናደደ፡፡
- የሚወጋውም ሰው ማን እንደሆነ በመገመት በፍጥነት ወደ ኋላ ለመማታት ወስነ፡፡
- ይህንኑ ለማድረግ በሂደት ላይ ሳለ ውስጣዊ ምልክት የሚወጋው ነገር ከምን የተከሰተ እንደሆነ እንዲመረምር አዘዘው፡፡
- ዞወር ብሎ ሲመለከትም አንዲት ልጃገረድ ቦርሳዋን ይዛ ከኃላ ቆመሰ አያት፡፡ እጅዋን በቦርሳዋ ላይ ስታስደግፍና ስታስነሳ የቦርሳን ጫፍ ላይ የሚገኘው ጠንካራ አካል ይወጋው እንደነበር ተመለከተ፡፡ እርስዋም ወዲያውኑ ጉዳዩ ምን እንደሆነ ሲገባት እጅዋን ሰበሰበች፡፡
- በክርኑ መቷቷት ቢሆን የሚከሰተው ምንድን ነበር - ነገሮች ሌላ መልክ ይይዙ ነበር፡፡

**ትዕግስት ወይም ጽናት ምንድን ነው?**

- ትግስት በዙሪያችን ወይም በርቀት በሚገኙ ክስተቶች የሚፈጠሩ ችግሮችን ለተወሰነ ጊዜ በመቋቋም በጎ በሆነ መልኩ በፍቅር ነገሮችን ተቀብሎ ማስተናገድ ነው፡፡
- የትዕግስትን አቅጣጫ መምረጥ ችግሮችን በመሰንበትት ለመፍታት ከመጥቀሙም በላይ ውጤቱም እጅግ የተሻለ ነው፡፡

# በፈጣኑ ዓለም ውስጥ የሚፈለግ ትዕግስት

**የትግስት ጥቅም ከቅዱሳት መጻሕፍት**

- ጌታችን ደቀመዛሙርቱን «ስለስሜ በሁሉ ዘንድ የተጣላችሁ ትሆናላችሁ እስከመጨረሻ የሚጸና እርሱ ግን ይድናል፡፡» አላቸው ***ማቴ 10፡22፡፡***
- በተጨማሪም «በሁሉም ስለስሜ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ ከሁላችሁም አንዲት ጠጉር እንኳ አትጠፋም በመታገሳችሁም ነፍሳችሁን ታገኛላችሁ፡፡» አላቸው፡፡ ***ሉቃስ 21፡16-19፡፡***
- ስለዚህ ሌሎች ችግር ሲያመጡብን መከራንም ሲያስከትሉብን ሳንጠላቸውና ሳንቆጣቸው መታገስ ሰማያዊ ጥበቃን የሚያስገኝ ሽልማት ነው፡፡ «ከራሳችሁም አንዲት ጠጉር እንኳን አትጠፋም - እስከመጨረሻው የሚጸና እርሱ ይድናል፡፡»
- ጌታችን ስለ ትዕግስትና ጽናት የነገረን ብቻ አልነበረም… ይልቁኑ በመዋዕለ *ሥጋዌው* በምድር በነበረበት ዘመን ሁሉ በሕይወቱ በተግባር ትእግስትና ጽናትን አሳየን እንጂ፡፡
- በለበሰው *ሥጋ* በቅድስና ሕይወት የሚገኘውን ትእግስት አሳይቶናል፡፡ ከሁሉም አቅጣጫ የነበረውን ጫና ወይም ግፊት ታግሶ ነበር፡፡
- አእምሮው የተነካ ነው ብለው የሚያስቡ ወዳጆች ነበሩት፡፡ ደቀ መዛሙርቱም እንደሞኝ በማሰቡ በምድር ላይ ንጉሥ የሚሆንበትን ዕድል አጣ እያሉ ያስቡ ነበር፡፡ በርሱም የሚደረግላቸውን መዳን ባለመሻታቸው በቅንአት ሊገድሉት በሚፈልጉ ፊት ዘመኑን ሁሉ ተአምራትን በማድረግ ምልክትን በማሳየት እንዲቆይ የሚሹ ተከታዮችም ነበሩ፡፡
- ጌታችን አምላካችንን የተቀበሉት እጅግ ጥቂቶች ነበሩ፡፡

# በፈጣኑ ዓለም ውስጥ የሚፈለግ ትዕግስት

- በነዚህ ሁሉ ግፊቶች መካከል ጌታችን የሰውን ዘር የማዳን ሥራውን ባለማቋረጥ በጽናት ይሰራ ነበር፤ የንጉሥ ሄሮድስን ጥላቻ ታግሷል ከሕጻንነቱ ጀምሮ ሊገድለ ይሻ ነበርና፡፡
- ሄሮድስን ወዲያው ሊያጠፋው የሚቻለው ሲሆን የትእግስትን፣ የመቻልንና የጽናትን ጎዳና በመምራት ከሄሮድስ ፊት ሸሸ፡፡
- የሰቀሉትንም ታግሷል፡፡
- ሁሉ ቢተውህም እኔ ግን አልተውህም ያለውን በኋላ በሴቲቱ ፊት የካደውን የቅዱስ ጴጥሮስን ክህደት ታግሷል፡፡
- ይሁዳ «የሰውን ልጅ በመሳም አሳልፈህ ትሰጠዋለህን በማለት የይሁዳንም ክህደትና አሳልፎ መስጠትም ታግሷል፡፡» ***ሉቃ 22፡48፡፡***
- ይህም ያሳየን የሰው ልጆች በመንፈሳዊነት ይዘውት ሊገኙ የሚገባ የትእግስት ደረጃ ነው፡፡
- ይህም ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው የእግዚአብሔር ልጆች በውስጣቸው በሚኖር በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የሚሳቡበት የተቀደሰ ማዕረግ ነው፡፡ « የመንፈስ ፍሬ ግን…» ገላ 5፡22-23፡፡
- እንደዚሁ በትግስትና ጽናት የሚሆኑ ሁለት የተለያዩ የትዕግሥት እሴቶች ይገኛሉ፡፡
    1. ለማንኛውም ሰው የሚሆን በማኅበራዊ ሕይወት የሚገኝ ትዕግሥት
    2. በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ለክርስቲያኖች የሚሆን መንፈሳዊ መሠረት ያለው ትዕግሥት
- በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ ስለሚገኝ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ስለተደረገው ሥራ ስንናገር የምንናገረው በቀላሉ ልንገልጸው የማንችለውን በዚያ ሰው ስላለ የተቀደሰ ሥራና ሥራውንም ስለሚሠራው ቅዱስ ኃይል ነው፡፡
    - ክርስቲያናዊ ፍቅር በሰው ሕይወት የሚገኝ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ነው፡፡ ይህም እጅግ ጥልቅ የሆነና በማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ ከሚገኝ ፍቅር ጋር የማናነጻጽረው ነው፡፡

# በፈጣኑ ዓለም ውስጥ የሚፈለግ ትዕግስት

- ደስታና ሰላምም በሰው የሚገኝ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ሲሆን ዓለም ለማንኛውም ሰው ከምትሰጠው ሰላምና ደስታ እጅግ የጠለቀ የራቀና የመጠቀ ነው፡፡
- እንደዚሁ እንደ መንፈስ ቅዱስ ፍሬ በእግዚአብሔር ሥራ በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ የሚገኘው ትዕግስት በዘወትር ሕይወታችን በማኅበራዊ ሕይወት ከምናካብተው የትእግስት ልምድ ይለያል፡፡

***<u>ከሰው የሆነው ትግስት ደረጃና ማህበራዊ አነሳሽ ምክንያቶቹ</u>***

- ትግስተኛ ሰው በማኅበራዊ ሕይወቱ ውጤታማና በሌሎችም የሚደነቅ ነው፡፡ ነገር ግን የትዕግስቱ መጠን ለማኅበራዊ ሕይወት ሲገመገም እያንዳንዱ ሰው ከሌላው ሰው ይለያያል፡፡

1. የሚናገረውን ሰው ተናግሮ እስኪጨርስ የማይታገሱት በቁጣ የማያቋርጡት ሰዎች ትዕግስት የሚደነቅ አይደለም፡፡ ነገሮችን ባለመናደድና ባለማዳነቅ መቆጣጠር ያንሳቸዋል፡፡ እንደዚህ ያሉ ሰዎች ትዕግስት የለሽ ናቸው፡፡
2. ከጠያቄ የቀረበላችውን ጥያቄ እስከመጨረሻው የመስማትና የመረዳት ትዕግስት ያላቸው ይህንም ምላሽ ከመስጠታቸው በፊት ብቻ የሚያደርጉት በእላፊ የተናነገረውን መብታቸው የተተነካበትን ኃይለ ቃል ግን መታገሉ የማይችሉ ሰዎች የትዕግስት ደረጃ አለ፡፡
3. ከኛ የሚበልጥ አቅም ያለው ( በቢሮ ያለ አለቃችን፣ በት/ቤት ያለ መምህራችን) በመሆኑ የተነሳ ኢፍትሐዊነትን ወይም በኃይል ለተደረገብን አጸፋ የማንመልስበት የትዕግስት ደረጃም አለ፡፡ እንዲህም ያሉ ሰዎች በቤት አብረው ለሚኖሩ ወይም ለቅርብ ጓደኞቻቸው ተመሳሳይ ትግስት ወይም መቻል የማያሳዩበት ሁኔታ ይገኝባቸዋል፡፡

# በፈጣኑ ዓለም ውስጥ የሚፈለግ ትዕግስት

**4.** ክፉ ቃላትን ወይም መጥፎ ድርጊቶችን በሌሎች ተፈጽሞብን የምንመልሰውን ወይም የምናደርገውን እስክናውቅ ጉዳዩ ግልጽ እስኪሆንልን ድረስ መልስ ሳንስጥ የምንቆይበት የትግስት ደረጃ አለ፡፡

5. ሕመምንና ሐዘንን እንዲሁም ከሕይወት የተለያየ አቅጣጫ የሚገጥመን ችግር የምንታገልበት የትዕግስት ደረጃም አለ፡፡ ለማይታገሱትና ቶሎም በጫናው ለሚጎዱት ደረጃ ቢኖርም ከችግሩ መቅለል የተነሳ ለመታየት የቻለ ትዕግስት ወዲያው የሚጠፋበትም ሁኔታ በቀላሉ ሊገጥመን ይችላል፡፡ በርግጥ ማንኛውም ሰው ሕመሙን እስከምን ደረጃ ድረስ ሊታገሰው እንደሚችል አያውቅም፡፡ ምክንያቱም በውስጡ መታወክ የተነሳ ስሜቱን ለጊዜው ለመደበቅና ጥንካሬውን ለማሳየት የሚችልበት አጋጣሚ ስለሚፈጠር ነው፡፡

6. ለረጅም ጊዜ ልታገሰው በሚል ሰበብ ባንዳንድ ጉዳዮች ለውሳኔ በመዘግየት የምናሳየው የትዕግስት ደረጃም አንዱ ነው፡፡ ትክክለኛው ምክንያቱ ለነገሮች ያለን ተቃራኒ አመለካከት ሊሆን ይችላል፡፡ ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን፡- በጎ ሥነ ምግባር ከሌላቸው ቡድኖች ከመራቅ ይልቅ እንዲለወጡ ተጨማሪ እድል ልስጣቸው በማለት ክፉ አመል ካላቸው መለያየትን የሚያዘገዩ ሰዎች ናቸው፡፡ ይህም ስህተት ነው፡፡ ምክንያቱም ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን ዓመል ሊያጠፋው ይቻለዋልና፡፡ ይህ ሰው ባመዘግየት እራሱን ከነዚህ ሰዎች መለየት ይገባዋል፡፡ ይህም ስለ ትዕግስት ከተናገርነው ጋር የሚጋጭ አይደለም፡፡

*ምን ተማርን*

1. ደስ በሚያሰኙ አጋጣሚዎች ሳንናደድና ሳንቆጣ ትግስትን ይዘን መገኘት እንደሚገባን፡፡

2. መዳናችን በትዕግስት እንደምንፈጽም እስከመጨረሻው ካልጸኑ ጀምሮ በማቋረጥ መዳን እንደማይገኝ፡፡

3. በምንኖርበት ማህበረሰብ ውስጥ በትዕግስት በመገኘታችን ክብርን የማግኘት ዕድል እንደሚኖረን ተምረናል፡፡

ይቀጥላል...

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org